# ደፋርና ጢስ

**ከዙዋይ ረዚን (ጄኔቫ)**
**እና**
**ከጋሜ ጎሹ (ኖርዌይ)**

በኢትዮጵያችን ውብ አነጋገር
መውጫ አያጣም አሉ ጢስና ደፋር
በር ቢቀረቀር ቢዘጋ መስኮቱ
ጭላንጭል ቢደፈን ጭቃ በምርጊቱ
ፍልጥ ቢደራረብ እንዲያይል ጉልበቱ
ብው ብሎ ቢነድ ግር እያለ እሳቱ
ሊያግደው አይችልም ጢስን ከመውጣቱ!
***

የጀግናም እጅእግሩን በሰንሰለት ቢያስሩ
እንዳይዘል በዙሪያው ገደል ቢቆፍሩ
በደንጋያ በብረት ቢብጅም አጥሩ
መትረየሱን ጠምዶ ቢታይ ወታደሩ
ፈርቶ አርፎ አይተኛም ካልወጣ ደፋሩ!
***

በዋና የሚሻገር ሃይለኛ ጅረት
የማይነቃነቅ ብርቱ እንደአለት
ሞገድ አሣላፊ የድልድይ አውታር
ክብሩ የማይለወጥ በወርቅ በብር
ለአገሩ ጠላት የማይበገር
ቆራጡ ደምመላሽ የቴዎድሮስ ዘር
በቁጣ እንፋሎት እየተቀቀለ
የጨለማ ጠላት ማሾ የመሰለ
በቀላል የማይወድቅ ዬትም ሆነ ዬትም
ጀግናው ያገሬ ልጅ እንደማር የሚጥም
በወኔ ታጅቦ እንደ እንግዳ ደራሽ
ከጠሩት የማይቀር ለሞት ሠርግ ምላሽ
ታች የማይገታ ካልወጣ እስከጫፍ
ፍፁም የማይደፍረው የማንም እንከፍ
በአንገት የሚጫወት እንደገና አሩር
ቁስሉን ጠግኖ በድግ በዝናር
ተቃጥሎ የሚነደው ባገሩ ፍቅር
ዛሬ ወዴት ጠፋ የቴዎድሮስ ዘር!

***

ተገንድሶ ቢወድቅ የሰማዩ ዓምድ
መሬት ቢንቀጠቀጥ ኮረብታው ቢናድ
ፈሪ መግቢያ ሲያጣ ፈልቶበት ረዓድ
ሰውን ከብቱን ቢጠርግ ጎርፍና ሞገድ
ንብረቱ ቢዘረፍ ብትከዳው ፍቅሩ
ጠላቶች ግራቀኝ እሱ ላይ ቢዞሩ
ከመጤፍ የማይቆጥር ጨክኖ ከልቡ
ጠላትን የሚያደቅ በፈረስ እርካቡ
ታጥቆ ቢመጣበት የማንም ወንበዴ
ነፍጥ ቢያነጣጥር ቢመዝ ጎራዴ
እንኳን ዱላ ሊይዝ እንኳንስ ከዘራ
ገደል የሚያገባው በአይን ውርወራ
የወኔ ተራራ የጀብዱ ጎተራ
አገሩ ስትማቅቅ እጅ እግሯን ታሥራ
ገላግሉኝ ልጆቼ ብላ ስትጣራ
ተገልባ በማፈር እራስዋን ስትደፋ
ክብርን የሚያለብሳት ወንድ ወዴት ጠፋ!
***

ክላሺን ፈርቶ ነው የቦምብ ፍንጣሪ?
ጥለውለት ይሆን ትንሽ ፍርፋሪ?
ከርቸሌ ገብቶ ነው ይዞት ፊርማቶሪ?
ቡኮ ሲያቀብል ነው ለአምባሻ ጋጋሪ?
ታዲያ ወዴት ጠፋ ወንዱ በፈጣሪ?
ወንድ ጠፍቶ እንጂ ነው ወንድማ ቢኖር
ባንዳ አገሬ አናትላይ አይወጣም ነበር!
***

ምነው ዛሬ ሆነ ደፋር ላይን ብርቅ
መሸሽን የማያውቅ ወይም መደበቅ
እንደዋዛ የሚያይ የወገቡን ትጥቅ
ሰውን የማይነካ አትንኩኝ ባይ እንጂ
የማይበረግገው ለጥይት ለፈንጂ
"የጀግና ልጅ እናት ታጠቂ በገመድ
ልጅሽን አሞራ እንጂ አይቀብረውም ዘመድ
ምነው ባደረገኝ የዚያ ደፋር እቱ
የምሥራች እንድል ገድሎ በመሞቱ"
እንደዚህ እያሉ በጋር በወንዙ
ይዘፍኑለት ነበር ለደፋር በብዙ!
***

ባንሆን ነው እንጂ የጀግኖቹ ፍሬ
መች ያረጥበን ነበር ፍርሃት እኛን ዛሬ

ቢነቀል ነው እንጂ የደፋሮች ችግኝ
አይረባም ነበረ ጉንዳንና ትንኝ
ጭቆና ጨምቆኝ በቀን ሳንቀላፋ
የሚቀሰቅሰኝ ደፋር እንዴት ይጥፋ?
***

አገር ሳይረገም በፊት ምነው በታነቀ
መሰቀሉ ላይቀር ያ በላይ ዘለቀ
"ወንድ አይብቀልብሽ" የሚል እርግማኑ
ቢደርስ ነው እንጂ በዚህ በዘመኑ
ምጥ ፈርታ ይሆን እንዴ የዛሬዋ እናት
ማርባት መጀመሯ ትልን ከእበት
ስልችቶች አባዩ የእበት ትራፊ
ያቦን መገበሪያ የበላ ቀጣፊ
ሞልቶ ተርፎ እያለ የሚያደገድግ
ሬሣ ፍለጋ ዋልኩ በየጥሻው ጥግ
ላገሩ የሞተውን ሳያፈገፍግ
አጥንቱ ነው በዬ ፍቱን መድኃኒት
በመቆፈር ላይ ነኝ የመቃብር ቤት
የቆመ ብፈልግ ወኔን የተካነ
የነገን አላውቅም ዛሬስ ራዕይ ሆነ!
***

እንዴት ይታዘበን ታጠቅ ቴዎድሮስ
ኢትዮጵያ ብቻዋን ቁማ ስታለቅስ
የሞቱለት አገር ሲፈረካከስ
እንዴት ይዘኑብን አቡነ ጴጥሮስ
ወንድ አጥልቶ ሲታይ የፍርሃት ቀሚስ
ምንኛ ይርገመን ዳኛው ምኒሊክ
ለኢትዮጵያ ጠላት ስንበረከክ
እኩል ሱሪ ታጥቃ ካባ ዳኛው ጋራ
ወንዱን የመራቺው በአድዋ ተራራ
ነፃ ሆኖ እንዲኖር ወገኗ እንዲኮራ
የእመቤቶች በላይ ደፋር ሴት ልጃቱ
እንዴት ትዘንበን እትዬ ጣይቱ
ምንኛ ይናደድ አሉላ አባነጋ
ኢትዮጵያን ሲያዋርድ የወያኔ መንጋ!
የቁጥሩን ብዛት ሳትመለከቱ
ሁለት ሶስት ሁናችሁ ጎበዝ መላ ምቱ
በኢትዮጵያችን ውብ አነጋገር
መውጫ አያጣምና ጢስና ደፋር

ጥሻውን እየጣስን ወደፊት ስንሄድ
ለተከታይ ብዛት ይጠባል መንገድ
***

ነጋሪት ይመታ አውጅ ይነበብ
ዳር እስከዳር ላለው የኢትዮጵያ ሕዝብ
"ፍፁም አታመንታ አትበል ነግ ዛሬ
ተነሣ ወሎዬ ተነሣ ጎንደሬ
አርሲና ኢሊባቦር ጎጃምና ሸዋ
ተነሱ ጃርሶዎች ጉርሱም ድሬዳዋ
ሐረርና ጂማ መራቤቴ ከፋ
ተነሥ የኢትዮጵያ ልጅ አገርህ ሳትጠፋ
ወያኔ ያጠረው የነገድ ክልሉ
በቶሎ ለማፍረስ ጎበዝ ተማማሉ
ኢትዮጵያ የወያኔ አትሆንም ባንቱስታን
ከቶ አንታዘዝም በከሃዲ ሥልጣን
ታጠቅ አታመንታ ይፋትና መንዝ
ከመዋጥ ተጠንቀቅ የነገድን መርዝ
አብቹና አንኮበር ሶዶና ወሊጋ
ይፋትና ሜጫ ሸንኮራና ቡልጋ
ደጅህን አይርገጥ የወያኔ መንጋ"!
***

ለሚያልፍ ሽቅርቅር ሳንስገበገብ
ለሚመጣው ትውልድ ካሁኑ እናስብ
ካልተነሳን በቀር በጥበብ በዘዴ
ሲያራብን ሊኖር ነው የማንም ወንበዴ
ካሁኑ እንዘጋጅ ካሁኑ እንጣር
መውጫ አያጣምና ጢስና ደፋር።
*****